# አማራ ይነሳል!



የአማራ ሰቆቃ ቁና ሞልቶ ፈሷል፣
ዛሬም ከርቸሌውን ጢም አርጎ ሞልቶታል፣
ተቤቱ ተባሮ ተመንገድ ዳር ወድቋል፣
ልጆቹ በጭራቅ በጅብ ታፍነዋል፣
ባለ እስተንፋስ ሁሉ በቃ ሊል ይገባል!

የእየሱስን እድሜ ግፍ ጽዋ ጨልጧል፣
ገደልነው ቀበርነው ብለው ፎክረዋል፣
ነገር ግን አማራ ሸቅብ ይተኮሳል!

ልክ እንደ ክርስቶስ በአንቀልባ ተሰዱል፣
ተሰፈር መንደሩ በሙርጅ ተጠርጓል፣
እንደ ማርያም ጠላት ተመንበር ተነቅሏል፣
በጦር በገጀራ ተወግቶ ተገሏል፣
ዳሩ ግን አማራ በሳልስት ይነሳል፣
ወደ ሰማይ ጉኖ ተመንበር ቁጪ ይላል።

ሄሮድስ እየሱስን በጣም ስለፈራው፣
ዘመቻውን ሲያውጅ አፍኖ ሊገለው፣
ህጻን ወንድ ልጆች ይረሸኑ እንዳለው፣
አማራን እንደ ነብር እንደ አንበሳ ፈርተው፣
ተምድር ሊያጠፉት በማደን ላይ ናቸው።

አብ ልጁን በምድር ፈተና እንደሰጠው፣
አማራንም አምላክ እየሞከረው ነው።

መቃብርን ፈንቅሎ ወልድ እንደተነሳው፣
አማራም ፈተናን በጥሶ አላፊ ነው።

ፍትፍት አጉራሹን ሕዝብ የከዳሃው ባንዳ፣
አገር ገንቢውን ሕዝብ የሸጥከው ይሁዳ፣
ሰላሳ ዲናርህን ለዘላለም ብላ!

ታረብ ተግብጠቹ እየዶለትክ ደባ፣
ተእጅ አዙር ቀኝ ገዥ እየፈተልክ ሴራ፣
አማራን ለመቅበር ሌት ተቀን ብትሰራ፣
ዳግም ላይሸወድ ቀጥ ይላል አማራ!

ክርስቶስ ንጉስ ነኝ የሚል ቃል ሳይወጣው፣
ፈሪስ ለቄሳሩ ዋሽቶ እንዳቃጠረው፣
ባንዳና ኸርማን ኮን አማራን የሚያማው፣
ንጉስ ታልሆንኩ ብሏል አማራ እያለ ነው።

የዚህ ዓይነቱ ሸውክ ደባውና አላማው፣
አማራን መስቀል ላይ በምስማር መምታት ነው።
አማራ በቅኔህ ሁሌ እንደምትለው፣
ለዱሩ ጸጥታ ነብሩ ቢታገሰው፣
ፍየል በምላሱ ላንቃውን ሞረደው።

ታሪክ እንደሚያውቀው አማራ ጽኑ ነህ፣
ልክ እንደ ክርስቶስ ዘመንም ቢከዳህ፣
ቀጥቅጠን ገደልነው ቀብረነዋል ቢሉህ፣
ፈንቅለህ ተነስተህ ድል ትቀዳጃለህ።

አማራ ሆይ አንተም አምልካህን እርዳው፣
ወንድምህ ሲያጠፋ ምከረው ውቀሰው፣
ዳሩ ግን በመጥፎ በክፉ ዓይን አትየው።

አማራ ጥፈቱ አንድ ብራና ነው፣
እንደ ጅል ቀዳደድህ መንደር አትጣለው።

በአማራ ሰቆቃ እጅግ የረካኻው፣
ገለን ቀብረነዋል እያልክ የምትዝተው፣
በገነባት አገር ኑሮን የነሳሃው፣
ክፋትህ ተንኮልህ የሰዶማውያን ነው፣
ገሞራው ሲያነድህ አማራ እሚድን ነው።

እንደ ዘጽአት ሕዝብ ቢፈስ ቢፈናቀል፣
እንደ ሰማእታት ቢገረፍ ቢታሰር፣
እንደ ክርስቶስ እጅ ቢመታበት ምስማር፣
እንደ ጎን አጥንቱም ቢጨቀጨቅ በጦር፣
ገለነዋል ብለው ቢቆፍሩም መቃብር፣
ድንጋዩን ፈንቅሎ አማራ ይነሳል!

ይነሳል!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥር ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.